homes victoria

50 Lonsdale Street,
Melbourne Victoria 3000
GPO Box 4057, Melbourne Victoria 3001
DX 210081

**OFFICIAL**

ነዋሪ
ኮሊንግዉድ በእግር የሚወጡ ህንጻዎች
ኮሊንግዉድ

ውድ ነዋሪ

ስለ ሆምስ ቪክቶሪያ ታልቁ የቤቶች ግንባታ (Big Housing Build) እድገት እና ስለ ሰማይ-ጠቀስ ፎቆች የመልሶ ማልማት መርሃ ግብር ያለው አዲስ መረጃ ለማሳወቅ እየጻፍንልዎት ነው።

የፕሮግራሙ ቀጣይ ምዕራፍ አሁን በ 7 አዳዲስ ቦታዎች በመካሄድ ላይ ነው። ይህ ማለት አሁን በ9 ሰፈሮች ወይም ሳበርቦች ውስጥ ለሚኖሩ የአሁን እና የወደፊት ነዋሪዎች የተሻሉ፣ ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ምቹ ቤቶችን እያቀረብን ነው። **የዛሬው ማስታወቂያ በቤትዎ ወይም በሕንጻዎ ላይ ተጽዕኖ አያሳድርም።**

## ዛሬ ይፋ የተደረገው ምንድን ነው?

ዛሬ፣ እነዚህን ሕንፃዎች እንደገና ስለማልማት ከነዋሪዎች ጋር ተነጋግረናል፦

- 25 እና 27 ኪንግ ስትሪት፣ ፐራሃን
- 150 ቪክቶሪያ አቬኑ፣ አልበርት ፓርክ
- 150 ኢንከርማን ስትሪት፣ ሴይንት ኪልዳ
- 159 ሜልሮዝ ስትሪት፣ ኖርዝ ሜልበርን
- 29 ክራውን ስትሪት፣ ፍሌሚንግተን
- 94 ኦርመንድ ስትሪት፣ ኬንሲንግተን

**ከጁላይ 2026 እስከ ፌብሩዋሪ 2028፣** መልሶ ማልማት በመካሄድ ላይ እያለ ወደ ተስማሚ ቤት እንዲሄዱ ለመርዳት ከእነዚህ ቤተሰቦች ጋር በቅርበት እንሰራለን።

## ወደ ሌላ ቦታ የሚዛወሩ ነዋሪዎችን ለመደገፍ በአቅራቢያ አዳዲስ ቤቶችን እየገነባን ነው

የእነዚህን ነዋሪዎች የመዛወር አማራጮችን ለመደገፍ ጥራት ያላቸው አዳዲስ ቤቶች በአቅራቢያው በግንባታ ላይ ናቸው። በዚህ አመት ሊጠናቀቁ ነው እነዚህም የሚከተሉትን ያካትታሉ፦

- ኤሴክስ ስትሪት፣ ፐራሃን
- ሲሞንስ ስትሪት፣ ሳውዝ ያራ

- ባራክ ቢኮን፣ ፖርት ሜልበርን
- ሆላንድ ኮርት፣ ፍሌሚንግተን

እነዚህ ቤቶች ለማሞቅ እና ለማቀዝቀዝ ቀላል ይሆናሉ፣ የመንቀሳቀስ ፍላጎት ላላቸው ሰዎች የበለጠ ምቹ ይሆናሉ፣ ደህንነትን፣ ብርሃን እና አየር ማናፈሻን ተሻሽሏል እንዲሁም በረንዳዎች እና የግል የልብስ ማጠቢያዎች ይኖራቸዋል።

## ስለ መልሶ ማልማት ፕሮግራም

የሜልበርን የቆዩ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ዘመናዊ የምቾት፣ የተደራሽነት እና የኃይል (ኢነርጂ) ቆጣቢነት ደረጃዎችን በሚያሟሉ አዳዲስ ቤቶች ይተካሉ።

እነዚህን ሕንፃዎች እንደገና በማልማት ነዋሪዎች ደህንነታቸው የተጠበቀ፣ ምቹ እና አሁን እና ወደፊት ለፍላጎታቸው ተስማሚ በሆኑ ቤቶች ውስጥ መኖር እንደሚችሉ እያረጋገጥን ነው።

ከጃንዋሪ 2028 በፊት የሚጀመር ተጨማሪ ከሰማይ ጠቀስ ፎቅ የማዛወር ሂደት አይኖርም።

## ወቅታዊ መረጃ እንዲደርስዎ ከኛ ጋር መገናኘትዎ አያቋርጡ

በእያንዳንዱ የፕሮጀክቱ ደረጃ ላይ ወቅታዊ መረጃ ለማቅረብ ከእርስዎ ጋር መገናኘታችን አናቋርጥም። እንዲሁም በአቅራቢያዎ ምን እየተከናወነ እንዳለ ለማየት እና የቅርብ ጊዜ ዜናዎችን እና ወቅታዊ መረጃዎችን ለመቀበል ለመመዝገብ homes.vic.gov.au ድህረ ገጻችንን መጎብኘት ይችላሉ።

ከሰላምታ ጋር

**Simon Newport**
ዋና ሥራ አስፈፃሚ
ሆምስ ቪክቶሪያ

28/01/2026